# ኦሮምያ - በብብቶቿ ፍምና ረመጥ የታቀፈች ምድር

ከበየነ ከበደ

ኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች የጋራ ሃገር ነች። ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የኦሮሞ፣ ሲዳማና አማራ ሕዝብ ይኖርበታል። የቱለማና ሜጫ ጎሳ የሆኑት ኦሮሞዎች ከምዕራብ እንጦጦ እስከ ባሮ ወንዝ ያለውን ምድር ይሸፍናሉ። በምዕራብ በኩል ከአዋሽ እስከ ባሮ በደቡብ ከአባይ ወንዝ እስከ ደቡብ ከፋ የሠፈሩት የኦሮሞ ምድር ነዋሪዎች ደጎችና ቅን ሰዎች ናቸው። ኦሮሞዎች መልካም ቤተሰቦች ናቸው። ኦሮምኛ በቶሎ ሊለመድ የሚችል ቀና ቋንቋ ነው። ቀደም ባሉት ጊዜዓት ቦረንቲቻና ቦረንቲቲ የተባሉት አድባሮች የኦሮም ሕዝብ ባህላዊ የአምልኮ ሥርዓቶች ሲሆኑ አትልዬ ሆራና አትልዬ ዱላ፣ ልጆች እንዲወለዱላቸው፣ ከብቶች እንዲረቡላቸውና መሬቱ እንዲለማ አምላካቸውን የሚማጸኑበት ባህል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ነጻነታቸው እንዲነፍጋቸው የማይፈልጉ፣ የማንንም የበላይ ጫና ሊሸከሙ የማይወዱ ደጎች ናቸው። ኦሮሞዎች በቶሎ ይቅር የሚሉ ቅኖችም ናቸው። አብዛኛዎቹ ኦሮሞዎች የክርስትና ወይንም የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ሆነዋል።

ይህን የመሰለ መልካም ባህል ያለውን የኦሮሞ ሕዝብ ከሌሎቹ ወገኖቹ ለይተው እንዳሻቸው ሊያሽከረክሩት የሞከሩት የአድዋው የባንዳ ልጆች ጥርቅም በእርግጥ ለጥቂት ዓመታትም ቢሆን ተሳክቶላቸዋል። የኦሮሞ ሕዝብ ነጻነቱን የሚወድ የበላይ አካል ጫናን የማይወድ ደግ ሕዝብ መሆኑን የተረዱት የአድዋ ባንዳዎች ኦሮምያን በክልል አጥረው ምድሪቱ ላይ ሳይንሳዊ አስተዳደር ዘይቤ እንዲጠወልግ፣ አዛዥና ታዛዥ፣ የበላይና የበታች መዋቅራዊ ሥርዓት እንዲጠፋ "እንኩ ነፍጠኞች የወሰዱባችሁን ነጻነታችሁን ተቀበሉን" ብለው አማለሏቸው። ተኩላዎቹ ህወሃቶች ሃገር ግንባታን፣ ድንበር ማስፋትን "አማራ" የሚል ስም በመስጠት ሕዝቡን አጥበው በሉት። ሕወሃት - በኦሕዴድ ሎሌዎቹ አማካኝነት መልካም አስተዳደርን አዛንፎ በደጋጉ የኦሮም ሕዝብ ላይ ሠፊ ሌብነት ፈጸመ። አባቱ የኢጣልያ ሻንጣ ተሸካሚና ፓስታ ቀቃይ የነበረው የባንዳው ነጋ ልጅ ስብኃት ባዋቀረው ርኩስ ሥርወ-መንግስት መሰሎቹን አሰበሰቦ በኦሮም ሕዝብ ላይ ለሶስት አስርት ዓመታት ቀለደ። ከሆሊውዱ ተዋንያን እኩል በምዕራቡ ዓለም በውድ መኪና የሚሽከረከሩት በአያቶቻቸው ባንዳነት የሚኩራሩት የሕወሃቱ ባንዳ ልጆች ምድር ጠቧቸው እንኳን በኢትዮጵያ መሃል የምትገኘዋን እቴጌ ጣይቱ የቆረቆሯትን የቀድሞዋ በረራ - አዲስ አበባን ይናፍቋታል። ጨዋዎቹ ልዕልት ዓይዳ ደስታም ሆነ ሂሩት ደስታ በዝግታ በሚራመዱበት ታላቁ ኢዮቤልዩ ቤተ-መንግሥት ውብ አዳራሽ እንዳሻቸው የደነሱት የባንዳ ልጆች - የጃንሆይን ወርቆች፣ የወርቅ ሳህኖች፣ ሹካዎችና ማንኪያዎች በእጃቸው ሳይነኩ አባቶቻቸው ወደ መቀሌ ፈረጠጡ። የመለስን፣ ስብሃትን፣ ስዩምን፣ አባይ ጸሃዬን፣ አዜብን፣ ወዘተ፣ ዓይን ጋርዶ ውድ የሆኑትን ወርቆችና ዘመናዊ ተሽከርካሪዎችን ያተረፈልን እግዚአብሄር ምን ይሳነዋል?

ሕወሃት በአንድ በኩል ሃገር ወዳዱን፣ ጀግናውን የአማራን ሕዝብ በስውርና ስውር ባልሆነ ዘዴ በዘር ፍጅት እያዳከመ በሌላ በኩል ደግሞ በኦሮምያ ምድር ላይ ሥርዓተ አልበኝነት አስፍኖ ቅሚያን፣ ስርቆትን፣ ሌብነትን፣ ውሸትን፣ ብልግናን፣ ወዘተ፣ እንደ ሥርዓት ገነባ። ሕወሃት ቀሪዎቹን ብሄር ብሄረሰቦች "አጋር" የሚል ስም ለጥፎላቸው አይዟችሁ "እናንተም ክልል ትሆናላችሁ" እያለ በቀቢሰ ተስፋ አደንዝዞ ትግራይን የመጨረሻው ምሽግ አድርጎ ሲዘርፍ፣ ገንዘብና ወርቅን በውጭው ዓለም ሲያከማች ቆየ። መልካምነትን ማውራት፣ ለተሻለ አሠራር መሚገት "የድሮ ሥርዓት ናፋቂ" በሚል ያስፈርጃል። "ነፍጠኛ" የምትለዋ ቃል የኦሮምያን ሕዝብ ማስደንገጫ ከበሮ ነች። የህብረተሰብ ሳይንስ ያለፈ ሥርዓት እንደማይመለስ ቢያስተምርም ቅሉ ባንዶቹ "የተወገደው ሥርዓት መጣብሽ" እያሉ

ኦሮምያን እሳተ ገሞራ አለበሷት። ቀድሞ በከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ውስጥም ቢሆን በትግል ስልት ሰበብ የተማሪዎችንና ምሁራንን አስተሳሰብ እያወላገዱ በርካታ ሻጥሮችን መፈጸም የቻሉ መሠሪዎች – የሚኒልክና ጎበናን ሃገር አቅኚነት - ቢያጣምሙ ምን ያስገርማል? የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም የክፋት ታክቲክና ስትራቴጂ በመዘርጋት ረገድ እንደ ሕወሃት ያለ አውሬ የትም የለም።

ሕወሃት ወደ መቀሌ ከፈረጠጠ በኋላ በኦሮምያ ያሉ የመንግስት ሠረተኞች እጅግ ደነገጡ። ሕዝባዊው ትግል ሌብነትን እያደከመ ሲሄድ ዝርፍያን የለመዱት ሁሉ ተሸበሩ። ትላንት ኩርኩር ገፊ የነበረ ሥርቶ አዳሪ አሆዲድን ተጠግቶ ሕንጻ አቁሟል። ትላንት ቤሳ ቤስቲን ያልነበረው ብልጣ ብልጥ ሚቴክን ተከልሎ አውሮፓዊ ሞዴል ቪላ ገንብቷል። የቀድሞዎቹ ኩርኩር ገፊና ብልጣ ብልጡ ብቻ አይደሉም - ዋልጌው ሥርዓት መጠውለጉን የተረዱ የመሸባቸው የኦሮምያ ሙሰኞች እጅግ እየተራወጡ ነው። ሙስና እየተቆለፈ መሄዱን የተረዱት ጉዳይ አስፈጻሚዎችም ቢሆኑ ናላቸው እየዞረ ነው። እንደው ሠይጣን ዓዕምሯቸውን ሸብቦት ነው እንጂ ሰው እኮ አንድ እንጀራ ይበቃዋል። በሙስና ቪላ የሚኖረው ሥርቆ-አደሩም ሆነ በላስቲክ ቤት የምትኖረው ደሃ ሁለቱም ይህችን ምድር ይሰናበታሉ። የሚገርመው ሥሮቆ ዱባይ ወይም አሜሪካ ከሸሸው ቀማኛ ይልቅ በደስታ የተሞላችው በላስቲክ ቤት የምትኖረዋ ምስኪን ሴት ነች።

ሕወሃቶች በብዙ ዋልጌዎች ስም ንብረት ገዝተዋል፣ ሕንጻ አቁመዋል፣ የንግድ ድርጅቶች መሥርተዋል። ነገ ከየት እንዳመጣው ማጣርያ አቅርብ መባሉ አይቀሬ መሆኑን የተረዳው የሕወሃት-ኦሆዲድ ሎሌ የሂሳብ ሰራተኛ ቀጥሮ የሃሰት ማወራረጃና ማስረጃ እየሠራ ነው። ውሉ አንዴ የተዛነፈ መዋዕለ ነዋይ በሃሰተኛ ሂሳብ ቀመር አይስተካከልም እንጂ ሞኞቹ የሌቦች አሽከሮ ከተጠያቂነት ለመውጣት ብዙ እየጣሩ ነው። "ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን አይደርጋል ድስቱን ጥዶ ማልቀስ" የምትለዋ በላስቲክ ቤት የምትኖረዋ ደሃዬቱ ሴት ነጻ ስትሆን በሌብነት በገዛው መኪና ውሃ ረጭቶባት ያለፈው ዋልጌ "ኃብታም " ግን እርሱ የሙስና ባርያ ነው። ባርያ ብዙ ዓይነት ገጽታ አለው። በሙስና የተገነባ ቪላና ሕንጻን ሊመርቅ የሄደው ሆዳምም ሆነ በሃሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተገኘ ማስትሬትና ዶክትሬት ግብዣ ላይ የተገኘው ሞኝ - ሁለቱም የሙስና አምላኪዎች ናቸው። "የሙስና አምላክ ሆይ - እኛንም ባርከን" ሊሉ አሸሼ ገዳሜው ላይ የተገኙት የምኞት ባርያዎች ያለፈው አለፈ ካሁን በኃላ ግን ሊማሩ ይገባቸዋል። አብዛኛው ራሱን ጠብቆ እንጂ ሙሰኞችን ተጠግቶ ባለሃብት መሆን አያቅተውም ነበር። እንደ ቀድሞዎቹ መልካም አስተዳዳሪዎችና ታታሪዎች በሃቅ መኖር እንጂ የሚያኮራው ሥርቆ መክበር ውጤቱ ሃገር ለቆ መፈርጠጥ አልያም ደብቁኝ ማለት ነው። ሥርቆ የሕዝብ ሃብት ዘርፎ የሚኮፈስ "ባለሃብት" ዛሬ የሰው ዓይን ሊያይ የሚችልበት ድፍረት የለውም። ዘራፊው ጨዋውን የኢትዮጵያ ሕዝብን ሊመለከት የሚችልበት ብሌኑ ሟምቷል።

ዛሬ ገንዘብ ተለውጧል። ሌቦቹ አሁንም ግራ ገብቷቸዋል። ገንዘቡን በወርቅ አልያም በንብረት ለመለወጥ ያደባሉ። አሁንም ደሆችን ሊይታልሉ ያስባሉ። ዛሬ ብዙ ሕንጻዎች ባለቤት አልባዎች ናቸው ይባላል። ሕወሃት ያበላሸው እየተመነጠረ - አስተዳዳሪ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ተቆጣጣሪ፣ ሠራተኛ እያለ ከላይ ወደ ታች የሚወርደው የአስተድደር ጠገግ ዳግም ይስተካከላል። አዛዥና ታዛዥ በመከባበር የሚያገለግሉበት እውነተኛው የፖሊስ ሥርዓት ዳግም ይገነባል። በኦሮምያ ምድር የሚኖረው ደግ ሕዝብ ተፈጥሯዊ ነጻነቱ ሊጎናጸፍ ጥቂት ይቀረዋል። በኦሮሞ ሕዝብ ስም ፓርቲ መሥርተው ለዘረፋ የተዘጋጁ ምሁር ተብዬዎች እንዲሁም ሥርዓቱን ተንጠላጥለው ያደፈጡ ሙሰኞችና ሃቀኛ ነጋዴውን የሚያዋክቡት ጉዳይ አስፈጽሚ ተብዬ ቀማኞችና የመልካም አስተዳደር ጠላቶች ጥግ ይይዛሉ።

የስብሃት-መለስ ሥርዓት አሁንም አድፍጧል። በአንድ ጥጋበኛ ባለሃብት የተዘጋው የሕዝብ መዝናኛውና ፈዋሹ ሶደሬ መፍትሄ ሳያገኝ የመለስ ፋውንዴሽን አስተዳዳሪ ሲመደብበት አይገባም። አማራና ኦርቶዶክስ ክርስትያኑ በቁሙ ሲቃጠል ንብረቶች ቤንዚን እየተርከፈከፈባቸው ቆሞ የሚመለከት ፖሊስና ከንቲባ ህጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል። መንግሥት እያለ ሕዝብ በሥጋት ሊኖር አይገባም። ቀድሞ ኮማድ ፖስት ታዞ ይቅርና አንድ ስኳድ ጦር ሲንቀሳቀስ አካባቢው ሰጥ ረጭ ይል ነበር። ያኔ እንኳንስ ሴት ተማሪዎች ሊታገዱ ይቅርና አንድ ባለ ሱቅ ቢዘረፍ አካባቢው ቀውጤ ይሆን ነበር። በንጉሡ ዘመን ጭቃ ሹሙ በደርግ ዘመን ደግሞ የቀበሌው ሊቀ-መንበሩ ሥርዓት ባስከበሩባት አገር ዛሬ ዕልፍ አዕላፍ አስተዳዳሪዎች፣ ከንቲቦችና ፖሊሶች በተመደቡባት ቤንሻንጉል ክልል ውስጥ በርካታ አማራ መታረዱና መፈናቀሉ የሁላችንንም ድክመትና ራስ ወዳድነት አጉልቶ ያሳያል።

ኦሮምያን መልካም አስተዳድር እንጂ ሙስና ሊገዛት አይገባም። ኦሮምያ ፍምና ረመጥ በብቶቿ አቅፋለች። መልካምነት ፍሙንና ረመጡን ከብብቷ ፈልቅቆ ያራግፈዋል። ቅንነት በኦሮምያ የተንሰራፋውን ብልሹ አስተዳደር ዳግም ይጠግነዋል። ኦሮምያ እብብቷ የሚነደውንውን እሳት አጥፍታ ግራ የገባው ሕዝቦቿን እንደገና በእቅፏ ሥር ልታደርግ ይገባል። በኦሮምያ ግብሩን ሊከፍል የሄደ ሃቀኛ ነጋዴ ሊጉላላ አይገባም። ኦሮምያ ውስጥ ቋንቋ አትችሉም ተብለው ሥራ የተከለከሉ ምሁራን ሁሉ መፍትሄ ሊፈለግላቸው ይገባል። ሃገሬ ብሎ የኖረ ዜጋ ሁሉ ባይተዋር ሊሆን አይገባም። እግዚአብሄር ሁሉን ይመለከታል። ኦሮምያ በስብሰባ ስም የምታወጣውን ከፍተኛ ገንዘብ ቀንሳ ለወጣቱ ሥራ መፍጠር ይገባታል። ሥራ አጥነት የሚፈጥረው አመጽ ትርፉ ለዘረፉ ለተዘጋጁ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ለሙስና አደሮቹ እንጂ ለደሃው ወጣት አንዳች አይፈይድም። የኦሮምያ ወጣት ንቃ፣ የዘራፊዎችና ቀማኞች ሥልጣን መወጣጫ መሰላል አትሁን። ሰው ተዘቅዝቆ የተገደላባትንና ንብረቶቿ እንደ ሶርያ አሌፖ የጋዩባትን ሻሸመኔን እንዲሁም ነገሌ ቦረናን እያሰበ በርካታ የኦሮምያ ነዋሪ ስጋት ገብቶታል። በሕወሃት ደጋፊዎች የሚመራውን ሥርዓተ አልበኝነትና አመጽ እየፈሩ ወደ ሌላ ቦታ የሸሹ መዋዕላ ነዋይ አፍሳሾች፣ ሥራ ፈጣሪዎችም ሆነ ወልደው የከበሩባት ነዋሪዎቿ ዳግም ወደ ቀያቸው እስካልተመለሱ ድረስ ስጋቱ ከሰዎች ዓዕምሮ ውስጥ አይወጣም። በምሽት ጨረቃ ደምቃ የምትታየው ኦሮምያ ዛሬ ቀትር ላይ ደብዛዛ ሆናለች። ዓለም አቀፍ ስጋት የሆነውን ኮቪድ በሽታ ተጨምሮ አመጽ ያስጋውን የኦሮምያ ነዋሪ የሚጽናናው እግዚአብሄር ቢሆንም እንኳን የመልካም ሰዎች አስተዋጾም ፍቱን መድሃኒት ነው።

ኦሮምያ ቀምኞችና ሙሰኞች ብቻ አይደለም ያቀፈችው። ኦሮምያ በሳል፣ ተራማጅ፣ ብቁና እጅግ ሃቀኛ ሙስና ጠል አስተዳዳሪዎች፣ ከንቲቦች፣ ፖሊሶች፣ የፋይናንስ ኃላፊዎች፣ አስተማሪዎች ወዘተ፣ አሏት። እነዚህ ናቸው እብብቷ ሥራ ያሉትን ፍምና ረመጥ የሚያጠፉት። እነዚህን ሃቀኞች ታሪክ ሲዘክራቸው ይቆያል።

ወልዶ ተዋልዶ አብሮ የኖረው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቱን በጋራ እየመከተ፣ ወንዞችን እየገነባ፣ ልማት እያነጠፈ፣ ቋንቋውንና ባህሉን እያሳደገ – ሆ - እያለ እየዘመረ ወደፊት ሊጓዝ ይገባል።

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ